# ዜና ስለ ራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት

ዜና ሰልፍ ሰፕላይ በየሁለት ወሩ አንዴ በ ሰልፍ ሰፕላይ ግብረ ሐይል በኢትዩጵያ አማካይነት የሚዘጋጅ ሲሆን ይህም ግብረ ሐይል በመንግስት ተቋማትና ከልማት አጋሮች የተወጣጣ ሮረም ነው፡፡ የጃይካ ዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት ዜና በማዘጋጀት ረገድ ቅድሚያውን ወስዷል፡፡

**ማውጫ**

- “ሰዎች ጥቅሙን ከተረዱ በፍፁም አያቆሙም ”

**ማስታወቂያ /መረጃ/**

- የተከናወኑ ክንውኖች እና በሚመጡት ሁለት ወራት የሚከናወኑ ድርጊቶች

**ከአቻ አጋሮች እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች**

- የውሃ ብድር ና ሰልፍ ሰፕላይ
- ሰልፍ ሰፕላይ አክሰሌሬሽን ዕቅድ
- የባለገመድ ፓምፕ ቴክኖሎጂ በሲ አሲ ስስተም የግምገማ አላማ
- የማነቃቂያ ስልጠና

## “ሰዎች ጥቅሙን ከተረዱ በፍፅም አያቆሙም”

“የሚጠቅሙ ቴክኖሎጂዎች ወደ ሕዝብ መድረስ ይገባቸዋል፡፡” ይላሉ አቶ አጥናፉ አስፋው ምክትል ቢሮ ኃላፊና የስ/ኃ/ል/ዋና የስራ ሂደት ባለቤት “እንደሌሎች በዋጋ ርካሽ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች ለምሳሌ እንደ የጠብታ መስኖ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ቴክኖሎጂው ለሕዝቡ የሚጠቅም ሆኖ ከተገኘ ያለምንም ማመንታት ቴክኖሎጂውን ሕዝብ ይቀበላል እንዲሁም ይጠቀምበታል፡፡ከራስ አገዝ ቴክኖሎጂዎች አንዱ የባለገመድ ፓምፕ በተመሳሳይ እንደዚሁ ነው፡፡” እንደ አቶ አጥናፉ ገለፃ የማንኛውም ምርት ውጤቶች ባለቤት እና ተጠቃሚው ህዝብ  እንጂ ግለሰቦች አልያም የቴክኖሎጂው ፈጣሪዎች መሆን የለባቸውም፡፡




በደቡብ ክልል ቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት ቢሮ ይህን የባለ ገመድ ፓምፕ ቴክኒካዊ የዕውቀት ሽግግር ላይ ከዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት በቅንጅት ከ6 የቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት ጋር ብዙ ተሞክሮዎችን ቀስሟል፡፡ አቶ አጥናፉ አስፋው በለው (Photo by JICA WAS-RoPSS)

አቶ አጥናፉም የቴክኖሎጂ ሽግግር የተደረገበትን መንገድ ያደንቃሉ፡፡የዕውቀት ሽግግር በቀጥታ ከታችኛው የህብረተሰብ ፍላጎትና አቅም ግንባታ ጋር የተገናዘበ ነው፡፡

ይህ ስራ ተኮር የትምህርት እና ስልጠና መርህ በብዙ መልኩ ለዘለቄታዊና ቴክኒካዊ የዕውቀት ሽግግር አስተዋፆ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መርህን በቀላል መልኩ ለባለ ገመድ ፓምፕ አምራቾች እና ለባለ ገመድ ፓምፕ ተካዮች እየተሰጠ ያለው የብቃት መለኪያ በጣም የሚያስደስት ነው ይላሉ አቶ አጥናፉ፡፡ ይህን የብቃት ማረጋገጫ ፈተና የደቡብ ክልል የብቃት ማረጋገጫ ተቋም ከክልሉ ቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት በቅንጂት እየተከናወነ የሚገኝ ጥረት ነው፡፡”አሁን አሁን ብቃት ያላቸው የባለገመድ ፓምፕ አምራቾችን እና ተካዮችን በቀላሉ ማግኘት ይቻላል ማለት ነው፡፡” ለብቃት ማረጋገጫው አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎች በብቃት ማረጋገጫ ማዕከል ከተዘጋጀ በኋላ ፈተናው እንዲሰጥ ሆኗል፡፡ተቀናጅቶ በመስራት ረገድ ስላለው ሁኔታ አስተያየታቸውን ሲሰጡም ከሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ወሳኝ መሆኑንም አስምረውበታል፡፡

በተለይም ለውሀ እና ግብርና መሰል ስራዎች ለቴክኖሎጂው ስርጭት ከፍተኛ አስተዋፆ አለው፡፡ በተለይም ስራው ከባለፉት ዓመታት ግምገማዎች በመነሳት እና ለስትራቴጂካዊ ዕቅድ ለማጠናከሪያ ስራው አስፈላጊ ነው፡፡በመጨረሻ አቶ አጥናፉ ሲገልጹ የልማት አጋሮች ከሆኑት እንደ ጃይካ ካሉ ድርጅቶች በከፍተኛ ግልፀኝነት እና ፍላጎት ለታችኛው ማህበረሰብ ቴክኖሎጂው እንዲደርስ በመደረጉ በከፍተኛ አድናቆት የምንመለከተው ነው፡፡ይህ ደግሞ በራስ አገዝ ስራዎች ላይ ያለውን ጥራት ዘለቄታዊነት በከፍተኛ ደረጃ የሚያረጋግጥልን ነው፡፡በማጠቃለያቸው አቶ አጥናፉ “ይህ የፕሮጀክት አንድ ቀን ቢቆምም ሰዎች ጥቅሙን ከተረዱ ስራው አይቆምም ፡፡” በማለት አስተያየታቸውን አጠናቀዋል፡፡

## የውሃ ብድርና ራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት



የአቶ ተፈራ ስመሮ ከላይ በፎቶው ላይ እንደሚታየው በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የውሃ ብድር ተጠቃሚ ናቸው፡፡ የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ደንበኛ ሲሆን የተበደሩትንም ገንዘብ በቤታቸው አቅራቢያ ለአዲስ መፀዳጃ ቤት ግንባታ ይጠቀሙታል፡፡

Water.org

“ዋተርዶት ኦርግ” የመንግስትን የንፁህ ውሃ አቅርቦትን ከሃይጅንና ሳንቴሽን ጋር በማጣመር የሚንቀሳቀስና  ሀገሪቱ ወደ መካከለኛ ገቢ ካለቸው ሀገራት ተርታ ለማድረስ የሚደረገውን ጥረት ከሚደግፉ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች አንዱ ነው፡፡

ወተር ዶት ኦርግ ከሦስት የአዋ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት/ማለትም ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ፣ ከአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም እንዲሁም ከቪዥን ፈንድ /ጋር በመሆን ቢያንስ 8000 የሚሆኑ የውሃ ብድር ተጠቃሚዎች ፒራሚዳዊ በሆነ ቅርፅ እ.ኤ.አ. በ2017 ለማዳረስ አቅዷል፡፡

ፕሮግራሙ የመንግስት የሰልፍ ሰፐላይ ስትራቴጂን ወደ ተግባር ለመተርጎም ከአጋር መስሪያ ቤቶች ማለትም ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ጋር በውሃ አቅርቦት ዙሪያ ብድርን የማመቻቸት ስራዎችን ተፈፃሚ ማድረግ ወይም በማዳበር ይሆናል፡፡

ድርጅቱ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትን በውሃ አቅርቦትና ንፅሀና ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶችን ጨምሮ የብድር አሰራር ሂደቶችን ለመቅረጽና ስለ ውሀ ብድር ቅርፃዊ ሂደት ስልጠናዎች ላይ የራሱን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

በተጨማሪም ከአጋሮች ጋር በመሆን የውሃ አቅርቦትና ንፅህና ብዙኑን ሕዝብ ለማዳረስ የሚደረገውን ጥረት ይደግፋል አብሮም ይሰራል፡፡

እንደ አለማቀፉ ጤና ድረጅት እና ዩኒሴፍ በጋራ ግምገማቸው ከአስሩ አንዱ ለንፁህ ውሃ እጥረት የተጋለጠ እና 1/3ኛው የአለም ህዝብ የመፀዳጃ ቤት አማራጭ የሌለው መሆኑን አረጋግጠዋል ፡፡እንደ መረጃው ከሆነ አብዛኛው ሰው የመፀዳጃ ቤት የሌለው ፣ ግን ደግሞ የተንቀሳቃሽ ስልክ ተጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል፡፡የአለም ኢኮኖሚክ ፎረም እ.ኤ.አ.በጃንዋሪ 2015 ባወጣው መግለጫ ከውሃ ንፅህና ጋር ያለው ቀውስ ቁጥር አንድ አለም አቀፍ አደጋ በማህበረሰብ ላይ መደቀኑን አስተዋውቋል፡፡

በኢትዮጵያ ደግሞ 88% ውሃን በሽክም ከተለያዩ ቦታዎች ወደየቤታቸው ይወስዳሉ፡፡ በኢትዮጵያ አብዛኛው ሕዝብ የራሱን የጉድጓድ ውሃ ለመገንባት የዝናብ ውሃን ለማጠራቀም ወይም መፀዳጃ ቤት ለመገንባት ተነሳሽነት ያለው ሲሆን ለውሃ ግንባታም ሆነ ለመፀዳጃ ቤት ግንባታ ስራዎች የብድር ድጋፉን የሚፈልጉ ናቸው፡፡

መንግስትም በነዚህ ስራዎች ዕውቅና እና ጠቀሜታ ዙሪያ ቁርጠኝነት ያለው ሲሆን በዚህም ቢያንስ አምስት የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ጥረቱን ለማገዝ ተቀላቅለዋል እንዲሁም የብድር አገልግሎቱን ለቡድን እና ለግል አመልካቾች ያቀርባሉ፡፡

የአስር ዓመታት የውሃ ብድር የስራ ልምድ ቀምሮ የውሃ ብድርን በአፍሪካ፣ ደቡብ ኢሺያ፣ በደቡብ ምስራቅ ኢሺያ ፣በላቲን አሜሪካ አገልግሎቱን ሲሰጥ የቆየው ወተር ዶት ኦርግ ፣ ሀገር ውስጥ ካሉ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ጋር በመሆን በኢትዮጵያ ተጠቃሽ የሆነ አስተዋፆ መንግስት ላቀዳቸው ግቦች እያበረከተ ይገኛል፡፡

በአለም ዙሪያ ከ 2.6 ሚሊዩን በላይ ሰዎች የንፁሁ ውሃ አማራጭ ያላቸው ሲሆን ከ600,000 ብር የውሃ ብድር ስርጭት ድጋፍ በወተር ዶት ኦርግ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪ “ወተር ዶት ኦርግ” አለም ላይ ካሉ ማይክሮ ፋይናንሶች ጋር በትብብር 128 ሚሊዮን የአሜርካ ዶላር ለንግድና ለማህበራዊ ኢንቬስትመንቶች ፈሰስ አድርጓል፡፡

ሰዎች በአለም ዙሪያ ለሚፈልጉት ነገር ብር ለመክፈል ፍቃደኝነቱ ካለ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ይህንን ዕድል እውን ለማድረግ አስተዋፆቸው ከፍ ያለ ነው፡፡

# የራስ አገዝ የውሃ ተቋማት ዕቅድ ዝግጅት

## IRC and Millennium Water Alliance

**በወረዳ ደረጃ በኢትዮጵያ የራስ አገዝ የውሃ አቅርቦትን ለማፋጠን በሚደረግ እቅድ፡ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ምንድናቸው**

አይ አር ሲ / IRC/ ከሚሊንየም ዋተር አሊያንስ/ Millennium Water Alliance/ና ከአጋሮቹ ጋር በጋራ በመሆን በሰባት ወረዳዎች በራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት ማፋጠንን አስመልክቶ እቅዶችን በማዘጋጀት ስራ ላይ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡



የዕቅድ ዝግጅት ውይይት በዱግዳ ወረዳ ኦሮሚያ /ፎቶ በአይ አር ሲ/

በዕቅድ ዝግጅቱ ላይ ከተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ማለትም ከውሃ፣ ግብርና/መስኖ ፣ጤና፣ የማይክሮ ፋይናንስ ከሴቶችና ህፃናት እና የወረዳ አስተዳደሮች የተገኙበት ነበር የዕቅድ ዝግጅቱ ከራስ አገዝ አንጻር አቅም ያለቸውን ቦታዎች መምረጥ ፤ በአቅራቢያ የሚገኙ የቴክኖሎጂ አማራጮችን ማቅረብ እና ፍላጎት የመፍጠሩን እንቅስቃሴ ማሳየት የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን የብድር አቅርቦትን እና የእርስ በእርስ ቅንጅታዊ አሰራሮችን መማማር ናቸው፡፡

**ምቹ የሆነ የፖሊሲ ሁኔታ**

የራስ አገዝ የውሃ ተቋማት ለመገንባት ምቹ የመንግስት ፖሊሲ እና ጥሩ አጋጣሚ እንዳለ ማየት ይቻላል፡፡በውሃ ዘርፍ 30% የውሃ አማራጭ የሌለውን የገጠር ሕዝብ በራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት ለመድረስ እንደ አንድ አገልግሎት ሰጪ ሞዳሊቲ እውቅና ተሰጥቶታል፡፡ ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች በሀገርና በክልሎች ደረጃ የተዘጋጀ ሲሆን ይህንኑ ጉዳይ እንዲከታተልልን አንድ ፎካል ሰው ተመድቧል፡፡በግብርና ዘርፍም ቢሆን የራስ አገዝ የውሃ ተቋማት ግንባታ አመታዊ የመሬት እና የውሃ ዘመቻ አንዱ አካል ነው፡፡

ይህም "አንድ የውሃ አማራጭ ለአንድ አባወራ" በሚል መርህ ሰዎች የራሳቸውን የውሃ አማራጮች በአባወራ ደረጃ ለአነስተኛ መስኖ እንዲገነቡ ይበረታታሉ፡፡ ይህ ስትራቴጂ በአባወራ ደረጃ በሀገሪቱ በተለያየ ጊዜ እየተከሰተ ያለውን የድርቅ ተጽዕኖ ለመቋቋም እንዲያግዝ ተደርጎ ተቀርጿል፡፡

**የውስጣዊ የየዘርፍ ቅንጅታዊ አሰራር ጉዳዮች**

በአባወራ ደረጃ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ባህል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡"አይ አር ሲ" ከሚሊንየም ወተር አሊያንስ ጋር በጋራ ባካሄዱት ቅድመ ጥናት እ.ኤ.አ 2015 መጨረሻ የጉድጓድ ውሃ ግንባታ በከፍተኛ ደረጃ ባለፉት 2-3 ዓመታት ውስጥ ፕሮግራሙ እየተካሄደ ባለባቸው ወረዳዎች በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል፡፡ሆኖም ግን አብዛኞቹ ጉድጓዶች ባህላዊ እና በሚገባ ያልተሸፈኑ ሆነው ምንም አይነት ቴክኒካዊ ድጋፍ ያልተደረገባቸው ናቸው፡፡ አንዳንዶቹም ወደ መፀዳጃ ቤት የተጠጉና የግል የአከባቢ ንፅህናውም ቢሆን ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ሆኗል፡፡በየዘርፉ ያለው የግብ ልዩነትም አንዱ ችግር እየሆነ መጥቷል፡፡

ለምሳሌ በውሃው ዘርፍ ጉድጓዶቹ በደንብ ተሸፍነው ለመጠጥ አገልግሎት እንዲውሉ ሲፈለጉ ፣ ግብርና በበኩሉ ደግሞ ለአነስተኛ መስኖ ከመጠቀም ባለፈ ትኩረት ሲሰጡ አይታይም፡፡ሆኖም ግን በቁጥር በዛ ያሉ የባለገመድ ፓምፖች ለብዙ አገልግሎቶች ማለትም ለመስኖ ፣ ለመጠጥ ውሃ ፣ ለከብቶች እና ለግልና አከባቢ ንፅህና አገልግሎቶች ውለዋል፡፡

የራስ አገዝ የውሃ ተቋማት ግንባታ ፕሮግራም ለባህላዊ ጉድጓድ ውሃ አቅም በፈቀደ መጠን በየጊዜው እየተሻሻለና እንዲያድግ ተደርጎ መገንባት ስለሚቻል ለተጠቃሚው የተለያዩ አማራጮችን ስለሚያቀርብ የሚበረታታ ቴክኖሎጂ አይነት ነው፡፡

የየዘርፎቹ ውስጥ የሚታዩ የቅንጅታዊ አሰራር በተለይም ውሃ እና ግብርና በራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት አሰራር ዙሪያ መግባባታቸው በጣም አስፈላጊና ዋነኛ ነው፡፡

**እመርታ የሌለው ድጎማ እና  የግል ዘርፍ ተሳትፎ ውስንነት**

የራስ አገዝ ስራዎች ዕቅድ ከምንም በላይ በአባወራ ደረጃ ግንዛቤ የመፍጠርና እና በራስ ፍላጎት እና ተነሳሽነት ሰዎች መዋለንዋያቸውን እንዲያፈሱ ማድረግን የካትታል፡፡ ፍላጎት እንዴት እንፍጠር የሚለው ውይይት እና በድጎማ ዙሪያ ያልተፈለጉ ውጤቶች መከሰታቸውን በግልጽ አሳይቷል፡፡በአባ ወራ ደረጃ የጉድጓድ ውሃ ግንባታዎችን ማካሄድ በግብረ ሰናይ ድርጅቶች እንደተጀመረና አንዳንድ የመንግስት መስሪያ ቤቶችም በሊጋስ ድርጅቶች እየተደገፉ መሰረታቸውን ይታወቃል፡፡ ይህም በሕዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ እና በፍቃደኝነት የመካፈል ፍላጎት ላይ ተጽዕኖ አሳርፏል፡፡መሰረታዊ የውሃ አቅርቦት አገልግሎቶች አቅርቦት በዋናነት ማረጋገጥ የመንግስት ሀላፊነት ነው፡፡በመሆኑም በአንዳንድ ወረዳዎች ድጎማ በማይደርግባቸው ፕሮግራሞች በአባወራ ደረጃ የገቢ መጠንን ወይም ሁኔታን ከግምት አላካተተም ፣ ስለሆነም ጥቅም ለማይሰጡ እና ለግብአት ብክነት አምርቷል፡፡

ጠንካራ የሆነ የግሉ ተሳትፎ በራስ አገዝ ምርቶችና አገልግሎቶች ዙሪያ አለመኖሩ ሌላው የውይይት ጉድይ እንደነበር በውይይት ላይ ተነስቷል፡፡ፕሮግራሙ ከሁሉም ወረዳዎች ለተወጣጡ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉ ሲሆን መንግስት የውሃ መውጫ ዕቃዎችን እና የውሃ



የእስቴ ወረዳ በዕቅድ ዝግጅት ላይ አማራ /ፎቶ በ አይ አር ሲ/



የፍርጣ ወረዳ በዕቅድ ዝግጅት ላይ /ፎቶ በ አይ አር ሲ/

ማጥሪያ ምርቶችን በገጠር ለሚገኙ አባወራዎች ለማሰራጨት ለመጀመሩ ዘላቂ የሆነ ፈንድ /fund/ ባለመኖሩ ምክንያት ችግር ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ይተመናል፡፡በተቃራኒው የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ በገጠር ከተሞች የራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት እና በየቤቱ የውሃ ማጥሪያ ቴክኖሎጂ የማድረስ ሂደቱን ሊጎዳ እንደሚችል ይታሰባል፡፡

በመሆኑም ምክንያት አባወራዎች ለአምራቾቹ የመክፈል ፍቃደኛነት እንዳይኖራቸው ያደርጋቸዋል፡፡

የራስ አገዝ የውሀ ተቋማት ግንባታ በወረዳ ደረጃ የመተግበር ዕቅድን በሌላ መልኩ እየሰሩ የመማር ሂደት ይሆናል ማለት ነው፡፡

መንግስትም በሂደት ላይ ምቹ ሁኔታዎች እየፈጠረና የራስ አገዝ የውሀ አቅም ግንባታዎች እንዲስፋፋና እንዲጎለብቱ የግሉ ዘርፍ በሰፊው እንዲሳተፉ ተግዳሮቶችን እንዲመቻቹና በሂደቱ ላይ እመረታ በማያሳዩ ፕሮግራሞች ላይ ድጎማውን በማንሳት ለዘላቂታማነቱ እንደመፍትሄ ቢወሰድ መልካም ነው፡፡

የራስ አገዝ የራስ ዕቅዶች በየወረዳዎቹ ዋሽ ፕሮግራም ውስጥ አንድ አካል በመሆኑ እንደ የወረዳዎች ነባራዊ ሁኔታ እየታየ መፍትሔ ቢሰጥበት የሚለው ሀሳብ በውይይት ላይ ቀርቦ ተሳታፊዎቹ ተወያይቶበታል፡፡

ለስኬታማነቱ በየዘርፉ የሚገኙ መስሪያ ቤቶች ቅንጅታዊ አሰራር ወሳኝ ሲሆን እስከ ታች ድረስ ያሉ የዘርፉ ተዋናዮች ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑም ተጠቋሚል፡፡ ለመርሀ ግብሩ ተፈፃሚነት ቁርጠኝነት ዋናው ጉዳይ ሲሆን በተለያዩ መልኩ የተገኙ ውጤቶችን ጠብቆ ለማቆየትም የሴክተሩ ተሳትፎ ውሳኔ የተገኙ ውጤቶች አመቱ መጨረሻ ላይ ይፋ የሚደረጉ ቢሆንም በአተገባበሩ ዙሪያ የመጡ ለውጦችን ሆነ ተፅዕኖዎች በ IRC እና በአጋሮቹ የሚገመገም ይሆናል፡፡

# የባለ ገመድ ፓምፕ ቴክኖሎጂ የዕውቀት ፍተሻ የብቃት ማረጋገጫ ማዕከል በኩል

JICA WAS-RoPSS

ብቁ የሆኑ የባለገመድ ፓምፕ አምራቾችን እና ገጣሚዎችን ማፍራት ለዋስ ሮፕስ ፕሮጀክት ገና ከጅምሩ አንገቡጋቢ ጉዳይ ነበር፡፡ለተለያዩ ሰልጣኞቹ ቴክኒካዊ ድጋፎች በፕሮጀክቱ አማካይነት ለአከባቢ ባለሙያዎች ለባለገመድ ፓምፕ አምራቾች እና ለባለ ገመድ ፓምፕ አሰልጣኞች የተሰጠ ቢሆንም በነዚህን ሰልጣኞች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የዕውቀት ደረጃቸውን ለመፈተሽ አልተቻለም፡፡

ይህም በመሆኑ ምክንያት ለመጀመሪ ጊዜ የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ለባለ ገመድ ፓምፕ አምራቾች ገጣሚዎችና ለአከባቢ ባለሙያዎች እ.ኤ.አ ሚያዝያ 9 እና 23 በ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የብቃት ማረጋገጫ ቢሮ በኩል ተሰጥቷል፡፡



የምሮቶች ምርመራ ሂደት በባለሙያዎች ግምገማ ሂደት ላይ በብቃት ማረጋገጫ ማዕከል ሐላፊዎች (ፎቶ በዋስ ሮፕስ)

በብቃት ማረጋገጫ መዕከል በኩል ሁለት ዓይነት የፈተና ዲዛይኖች የቀረቡ ሲሆን ፈተናውንም ለአምራቾች እና ለገጣሚዎች ብቻ ለብቻ የቀረበ ነበር፡፡

ከፈተና በፊት የስልጠና ዕቃዎች በፕሮጀክቱና በቴክኒክ እና ሙያ ማዕከል በኩል እንዲቀርብ የተደርገ ሲሆን ፣ ወደ 10 ለሚጠጉ አምራቾች እና ለ27 ገጣሚዎች ፈተናውን በሚገባ ያለፉ ሲሆን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬትም ተሰጥቷቸዋል፡፡በተለያየ መስክ በፈተናው ተሳታፊዎች የተሳትፎ ሰርተፍኬት የተሰጠ ሲሆን በሰርተፍኬት ደረጃ የተሳተፉ አቅማቸው እና ሙያዊ ችሎታ ደረጃቸውን አይተውበታል፡፡በመሆኑም የብቃት ማረጋገጫ የባለገመድ ፓምፕን የዕውቀት ሽግግር ዙሪያ መሰጠቱ ድረጃውን እና ጥራቱን የጠበቀ ምረት ለማምረት ትርጉም ይሰጠዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

የዋስ ሮፕስ ፕሮጀክት ቡድን እንነዚህን ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ሀይል ባለሙያዎች በማስተዋወቅ ረገድ ድጋፍና አስተዋፆ አድርጓል፡፡ የመንግስት ቢሮዎች እና ልማት አጋሮች ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት ለማግኘት እነዚህን አምራቾች እና የባለገመድ ፓምፕ ገጣሚዎች እንዲጠቀሟቸው ይበረታታል፡፡





እ.ኤ.አ ሚያዝያ 9 2016 በሰላም ሐዋሳ ለአምራቾች (በስተቀኝ) እና ለተካዮዎች (በስተግራ) ሚያዝያ 23 በቴክኒክ እና ሙያ ተቋም ማዕከል (ፎቶ በዋስ ሮፕስ)

# ለአከባቢ ባለሙያዎች የተሰጠ የማነቃቂያ ስልጠና

ሁለት የማነቃቂያ ስልጠና ለአከባቢ ባለሙያዎች በዋስ- ሮፕስ ፕሮጀክት አማካይነት በመስቃንና በዳሌ ወረዳዎች በአውሮፓዉያኑ ቀመር አቆጣጠር በመጋቢት እና ሚያዝያ 2016 ተሰጥቶ ነበር፡፡

እነዚህ የአከባቢ ባለሙያ ለተመረጡ ሰዎች የቴክንካዊ ሙያ አገልግሎት ለባለ ገመድ ፓምፕ ተጠቃሚዎች በመንደር ደረጃ አገልግሎቱን የሚሰጡ ሲሆን ለአንድ ሳምንት በቆየው ስልጠና ሙያቸውን የሚያሻሻሉበትና ሙያዊ ክለሳ ያደርጉበት ተከላና ጥገናን የወሰዱበት ስልጠና ነበር፡፡

በዳሌ ወረዳ በተደረገው ስልጠና የሁለት ቀን የአሰልጣኞች ስልጠና የክልሳ እና የማነቃቂያ ስልጠና ለቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት በተጓዳኝ ተሰጥቷል፡፡

ተሳታፎዎቹ የቀድሞ ዕውቀታቸውን የፈተሹበት እና የቡድን ውይይት ለባለገመድ ፓምፕ ቴክኖሎጂ ስርጭት ዙሪያም ውይይት ያደርጉበት ነበር፡፡



ከተከላ በኃላ የገመድ ፓምፕ ምርመራ ሲካሄድ(ፎቶ በዋስ ሮፕስ)

ሁለም ተሳታፊዎች በዚህ ማነቃቂያ ስልጠና ዙሪያ እርስ በእርሳቸው የልምድ ልውውጥ ያደረጉበትና ሐሳብ የተለዋወጡበት ነው፡፡ ስልጠናው ወንድማዊ የሆነ ግንኙነታቸውን ለማጠንከር እና የስራ ግንኙነት ለመመስረትም ዕድል ሰጥቷቸዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ሚያዝያና ግንቦት 2016 የተከናወኑ ክንውኖች

| | |
|---|---|
| ኤፕሪል4 | የራስ አገዝ ግብር ሀይል ስብሰባ |
| ኤፕሪል 4-9 | የባለ ገመድ ፓምፕ የጥራት ቁጥጥር ስልጠና ለአምራች /ጃይካ ዋስ ሮፕስ/ |
| ኤፕሪል 9 | የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ለባለ ገመድ ፓምፕ አምራቾች /ጃይካ ዋስ ሮፕስ/ |
| ኤፕሪል18-23 | ለአከባቢ ባለሙያዎች የሚሰጥ የማነቃቂያ ስልጠና /ጃይካ ዋስ ሮፕስ/ |
| ኤፕሪል 21-22 | የ ቲኦቲ ክለሳ/ጃይካ ዋስ ሮፕስ/ |
| ኤፕሪል 23 | የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ለአከባቢ ባለሙያዎች |
| | - ሚሊኒየም ዋተር አሊያንስ ፕሮጀክት ማንጅመንት የግሩፕ ስብሰባ የራስ አገዝ አክስሌሬሽ አተገባበር አጋሮች |
| | - የፍላጎት መፍጠሪያ በአባወራ ደረጃ ከራስ አገዝ አጋሮች ጋር ሚሊንየም ዋተር አሊያንስ |
| | - ማህበረሰብ አቀፍ ስብሰባዎች በባለ ገመድ ፓምፕ የማስተዋወቅና መትከል ለአከባቢ ባለሙያዎች /ጃይካ ዋስ ሮፕስ/ |

## ቀጣይ እውኖች ለሰኔ እና ለሐምሌ 2016 ወራቶች

| | |
|---|---|
| | - የራስ አገዝ ግብረ ሐይል ስብሰባ |
| ጁን 12-30 | የተርሚናል ኢቫሌዮሽን ሚሽን /ጃይካ ዋስ ሮፕስ/ |
| ጁን | የባለ ገመድ ፓምፕ ተካዮች ስልጠና በሐዲያ ዞን በደቡብ ክልል የባለ 10000 የባለ ገመድ ስርጭት ድጋፍ /ጃይካ ዋስ ሮፕ ፕሮጀክት/ |

If you have any comments, questions, suggestions, please contact us at;
JICA WAS-RoPSS Project
Room # 012, Ministry of Water, Irrigation and Electricity
Tel: +251 - (0)11-651-1455
Mob: +251 - (0)935-353210/12/14
E-mail : jica.ropepump.ethiopia@gmail.com
http://www.jica.go.jp/oda/project/1100485/index.html (jp)
http://www.jica.go.jp/project/english/ethiopia/004/index.html (en)

Websites
MoWIE http://www.mowr.gov.et/
CoWASH http://www.cmpethiopia.org/
IRC http://www.ircwash.org/
Aqua for All http://www.aquaforall.org/
Water.Org http://water.org/
Rural Water Supply Network
http://www.rural-water-supply.net/en/resources/details/662